

# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ የዐቢይ ጾም (፫ኛ)

[፫፻፷፯ኛው እንጀራ] ሳምንቱ - ዘወረደ የካቲት ፯ ፳፻፱



ወደ እግዚአብሔር በንስሐና በቁርባን ለመቅረብ - ”ዘመቻ ነፍስ” - የተቀደሰው ታላቁ የጌታ ጾም (ማቴዎስ ፬)።

ጽድቅን
የሚራቡና
የሚጠሙ
ብፁዓን ናቸው፥
ይጠግባሉና።

ማቴዎስ ፭፡፮

በኃጢአትህ አስቸገርኸኝ፥
በበደልህም አደከምኸኝ።
መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ።
ኃጢአትህንም አላስብም።

ኢሳይያስ ፵፫፤ ፳፬-፳፭

አያሌ ቀንም
አዝን ነበር
በሰማይም
አምላክ ፊት
እጾምና እጸልይ
ነበር።

ነህምያ ፩፡፬

## በዚህ ቀን ከሚታሰቡት መካከል

ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን የቀባችው ሴት እረፍት (ማቴ ፳፮-፮-፲፫) ስሚም ማርያም ነው።

## ለማወቅና ለማድረግ

ዐቢይ ጾም (ከየካቲት ፩ እስከ መጋቢት ፳፮) ፶፭ ቀናትን ሲይዝ እነዚህም በቅደም ተከተል፤

፩) ጾመ ሕርቃል (ሙሴኒ) - ፯ቀን

፪) የጌታችን ጾም (ጾመ ኢየሱስ) - ፵ ቀን

፫) ሰሙነ ሕማማት - ፯ ቀን ናቸው።

ዐቢይ ጾም የየራሳቸው መጠሪያና ምክንያት ባላቸው በ፰ ሳምንታት (ከእሁድ እስከ ቅዳሜ) ይከፈላል። እነዚህም ከዛሬ ጀምሮ ዘወረደ፤ ከዛ ቅድስት ፤ከዛ ምኩራብ ፤ከዛ መጻጉዕ ፤ከዛ ደብረ ዘይት፤ ከዛ ገብር ኄር ፤ከዛ ኒቆዲሞስ፤ ከዛ ሆሳዕና (ሰሙነ ሕማማት የሚጀምርበት)።

ዘወረደ - ከጌታችን በቀር ከስማይ የወረደ(የመጣ) ወደሰማይም በሥልጣኑ የሚወጣ የለም።